***ለ"ፍትህ"፣ ለ"ነፃነት" እና ለ"ዴሞክራሲ" እንታገላለን የሚሉት ቡድኖች በቅድሚያ ከስሞቹ ትርጉም ጋር ይታረቁ!***

ፍትህ፣ ነፃነትና ዴሞክራሲ ማለት የሚያማምሩና የተከበሩ ስሞች ናቸው። እነዚህ የተከበሩና የተቀደሱ ስሞችን መጠሪያቸው ያደረጉ ኣንዳንድ ወገኖች ግን ከስሞቹ ትርጉም በተቃራኒ ተሰልፈው መገኘታቸውን በገሃድ እየታዘብን ነው። የኢትዮጵያን ኣንድነት ለመጠበቅ ቆመናል የሚሉት እነዚህ ወገኖች ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ እንታገላለን እያሉን በተግባር ግን ፀረ ፍትህ፣ ፀረ ነፃነትና ፀረ ዴሞክራሲ መሆናቸውን ለማስመስከር እየተጉ ናቸው። እንደዚህ ያሉት ቡድኖች ምኞታቸው ከቶ ሊሰምርላቸው ስለማይችል ኣንድን ስም ይዘው ለረጅም ጊዜ በህዝብ ልብ ውስጥ ቦታ ኣግኝተው መሰንበትም ኣይችሉም። ፈረንጆቹ "*ባዶ በርሚል የበለጠ ይጮሃል*" እንደሚሉት ከጩኼታቸው በስተጀርባ ጉዋዳቸው ሲታይ ባዶ ነው። ይህ ደግሞ የሰፊው ህዝብ ድጋፍ እጥረት ያላቸውና ለህዝቦች መብት ተገቢውን ቦታ የማይሰጡ ሃይሎች ኣንዱ መለያ ምልክታቸው ነው።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ትላንትም ዛሬም የህዝቦችን መብቶች ለመጨፍለቅ ከሚመኙ ኣንዲህ ካሉት ወገኖች ጋር ሙግት ገጥሞ ጊዜውን የሚያባክንበት ምክንያት የለውም። በኦሮሞ ህዝብና በኦሮሞ ብሄረተኛነት ላይ ኣነጣጥረው የሚያሰሙት የቁራ ጩኼታቸው ሲበረክት ግን በዚህ ምክንያት ለሚባክነው ጊዜና ጉልበት እያዘነ መካድ የማይችሉትን ሃቆችን እየመረራቸውም ቢሆን ሊያስታውሳቸው ይገደዳል። የኦሮሞ ነፃነት ግንባር "ነፃነት" የሚለውን ኣላማውን ኣንግቦ ለተደራጀለት ህዝብ መታገሉ ሃጢያት ኣይደለም። "ነፃነት" የሚለውን ክቡር ስም እንዲያው ለይስሙላ በመጠሪያ ስማቸው ውስጥ ኣካትተው እየተጠሩበት መለስ ብለው ደግሞ "ለምን ለነፃነትህ ትታገላለህ?" ማለት የሚዳዳቸው ወገኖች በቅድሚያ ከህሊናቸው ጋር ይታረቁ እንላለን።

ኦነግ የሚታገልለት ነፃነት እነሱ ለማማለያ ብለው በስማቸው ላካተቱት ኣይነት የይስሙላ ነፃነት ሳይሆን ለትክክለኛው የነፃነት መብት መሆኑን ይረዱ። ኦሮሞ በህዝብነት ተደራጅቶ ራሱን ከጥቃት እንዲከላከል ያስገደደው ትላንት ኣባቶቻቸው በህዝቡ ላይ የፈፀሙት ታሪክ የማይረሳው የከፋ ግፍና በደል መሆኑ ቢገባቸው መልካም ነው። እነዚህን ስብስቦች ከሚመሩና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው በኦነግና በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ላይ የጥቃት እጃቸውን ከሰነዘሩት ግለሰቦች ኣንዳንዶቹ ቀደም ሲልም በወያኔ ኢህኣዴግ ውስጥ ተሰልፈው ተመሳሳይ ፀረ ኦሮሞ ህዝብ ትግል ዘመቻ ላይ ሲሳተፉ እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ታሪካቸው ምስክር ነው። ዛሬ "ፍትህ" "ነፃነት" እና "ዴሞክራሲ" የሚሉ ስሞችን ለጥፈው በወያኔ ተቃዋሚነት ብቅ ቢሉም ምንም ኣይነት የኣቋዋምና የፖለቲካ ኣመለካከት ለውጥ የላቸውም።

ዛሬ የኦሮሞ ህዝብ ንቃተ ህሊና ጎልብቶና የብሄረተኛነት ስሜቱም ሊቀለበስ ከማይችልበት ደረጃ መድርሱ እነዚህን ወገኖች እንቅልፍ እንደነሳቸው ይገባናል። ኦሮሞ ካሁን ወዲያ ለማንኛውም ምድራዊ ሃይል የማይንበረከክና በማንኛውም እኔ ኣውቅልሃለሁ ባይ ሃይል ስር መገዛትን እንደማይፈቅድ መረጋገጡ የእግር እሳት

እንደሆነባቸው በገሃድ እየታየ ነው። በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚያወግዙ ኣስመስለው “*ዘረኛ*” “*ጎሰኛ*” ሲሉ ወያኔን ብቻ ሳይሆን በብሄሩ የተደራጀውን ኦነግንና የኦሮሞን ህዝብ እንዲሁም ሌላውንም ጭምር እየዘለፉ መሆኑን ለመረዳት ኣያዳግትም። “*ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ*’ እንደሚባለው መሆኑ ነው። ይህም ከተሰፋ መቁረጥ ስሜት የሚመነጭ ዘለፋ መሆኑ በይፋ ይታያል። “ብሄርተኛ” እና “ጎሰኛ” በሚሉት ስያሜዎች መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት እንኩዋን ኣይገባቸውም ወይንም እንዲገባቸው ኣይፈልጉም። የብሄረተኛነት እንቅስቃሴ ከወያኔ ስልጣን መያዝ በሁዋላ የተከሰተ ይመስል በብሄሩ የሚደራጀውን ወገን ሁሉ ጎሰኛ፣ ዘረኛ፣ ጠባብ እያሉ ሁሉንም ከወያኔ ጋር መወንጀልን መለያቸው ኣድርገዋል። ራሳቸውን “ኢትዮጵያዊነት” በሚለው የማስመሰያ ለምድ ሸፍነው የኣንድን ብሄር የበላይነት የሚያቀነቅኑ የከፉ ዘረኛና ጎሰኛ ቡድኖች መሆናቸው እየታወቀ በብሄራቸው ስም በይፋ የተደራጁትን ሃቀኛ ወገኖች በዘረኛነት መውቀሳቸው በርግጥ ኣስነዋሪ ነው።

“*ፍትህ*’ “*ነፃነት*” እና “*ዴሞክራሲ*” የሚሉ የማማለያ ስሞችን ግንባራቸው ላይ ለጥፈው የኢትዮጵያ ህዝቦችንና ኣለም ኣቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር ደፋ ቀና የሚሉት እነዚህ ወገኖችና ኦሮሞን ጨምሮ የሃገሪቷ ህዝቦች ያላቸው ራእይ ሆድና ጀርባ ነው። እነርሱ የህዝቦችን ማንነት ኣምና የማትቀበለዋንና የኣንድ ብሄር የበላይነት ስልታዊ በሆነ መልኩ የታደሰባትን ኢትዮጵያ ለማየት ይመኛሉ። ኦሮሞው እንደ ኦሮሞነቱ፣ ኦጋዴኑ እንደ ኦጋዴንነቱ፣ ሲዳማው እንደ ሲዳማነቱ፣ ትግራዩ እንደ ትግራይነቱና ሌሎች የሃገሪቷ ብሄር ብሄረሰቦችም እንደማንነታቸው ተደራጅተው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ጥያቄ እነዚህ ወገኖች ዘንድ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም። ለዚህም ሲባል የስንት ጀግኖች ደም የተከፈለበትንና ዛሬም እየተከፈለበት የሚገኘውን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ለመፋቅ እየደከሙ ናቸው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የህዝቦችን መብቶች የተቀበሉ ኣስመስለው ኣፈ-ቂቤ ሆደ-ጩቤ በመሆን ኣንዳንድ የዋህ የብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን ለማማለል ያደረጉት ጥረት ከሽፎባቸዋል። ነገም ቢሆን በዚህ ኣይነቱ ኣካሄድ ሊሳካላቸው እንደማይችል እንነግራቸዋለን። እኔ ኣውቅልሃለሁ በሚለው ብልጣልጣዊ ኣካሄዳቸው የህዝብ መብት ፀሮች መሆናቸውን ራሳቸው በገሃድ ኣስመስክረዋልና ካሁን ወዲያ ህሊና ያለው ዜጋ ሊታለልላቸው ኣይችልም። እስካሁን በጥቂቱም ቢሆን ተታልሎላቸው የነበረ ወገንም ዛሬ ኣይናችሁን ላፈር ብሎ ራሱን ከነርሱ በማራቅ ላይ መሆኑ የኣደባባይ ምስጢር ነው።

የድርጅታቸው ስያሜ ተቃራኒ መሆናቸውን ያስመሰከሩት እነዚህ ወገኖች እውነተኛውን ማንነታቸውን ኣሳምረው የሚያውቁትን እንደ ኦነግ ያሉ ሃይሎችን ሲያወግዙ “*ስለድርጅታችን ማንነት ግንዛቤ የሌላቸው ጥራዝ ነጥቆች*” እያሉ ከማብጠልጠል ኣልፎ ስድብ ይዳዳቸዋል። “የድርጅታቸው ማንነት ግንዛቤ” ግን በውጭ ምንዛሬ የሚገዛ ውድ ምስጢር ሳይሆን በገሃድ የተጋለጠ ነገር ነው። እነርሱ ማለት የህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጨርሶ ኣንቀበልም የሚሉት ናቸው። እነርሱ ማለት በሪፈረንደም የራስን እድል መወሰን ቀርቶ በብሄሮች ማንነት ላይ የተመሰረተውን ወይም ወደፊት የሚመሰረት ፌደራላዊ የመንግስት መዋቅር ከቶ ኣንቀበልም የሚሉን ጉደኞች ናቸው። እነርሱ ማለት ከኣንዲት ባንዲራ በስተቀር የህዝቦች ነፃነት ኣርማ የሆኑ ባንዲራዎችን

ማየት ኣንፈልግም፣ ከኣማርኛ በተጨማሪ ኣፋን ኦሮሞም ብሄራዊ የስራ ቋንቋ ይሁን በሚሉት ሃሳቦች ራሳችንን ማታለል ኣንሻም እያሉን ያሉ ወገኖች ናቸው። እነርሱ ማለት ሌሎችንም ተመሳሳይ ፀረ ህዝቦች መብት እርምጃዎችን የመውሰድ ራእይ ይዘው የተነሱ ናቸው። ይህ እንዲያው በጭፍኑ እነርሱን ለመወንጀል ተብሎ በኣሉባልታ የሚነገር ወሬ ወይም በነርሱ ቋንቋ "*ጥራዝ ነጠቅ*"ነት ሳይሆን በተጨባጭ ማስረጃዎች የተደገፈ ሃቅ ነው። ሌላው ቀርቶ ከፍተኛ የኣመራር ኣባሎቻቸው ሳይቀሩ ይህንን ኣላማቸውን በገሃድ ሲናገሩ ተመዝግቧል። ከዚህ በላይ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ኣስፈላጊም ኣይመስለንም። ባጭሩ እያሉን ያሉት የተደራጃችሁለትን ኣላማ ትታችሁ እኛ ስር ግቡ ከማለት ውጪ ሌላ ትርጉም ያለው ኣይደለም።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባርና የኦሮሞ ብሄረተኞች እነዚህ ወገኖች በሚወቅሷቸው መልኩ ከሙታኖች ጋር ኣይደለም ትግላቸው። "*የታሪክ እስረኞች*" መባልም ባልተገባቸው ነበር። "ፍትህ" "ነፃነት" እና "ዴሞክራሲ" እያሉ የሚዋሹን ወገኖች ኣባቶቻችን ትላንት ያቆሰሏችሁን ቁስል እርሱና ጭጭ በሉ ሲሉ ማፈር ነበረባቸው። እንዲህ ማለት ኣይሁዶችን *የሆሎከስቱን* ጭፍጨፋ እርሱና ከናዚዎች ስር ሰጥ ለጥ ብላችሁ ተገዙ ከማለት የተለየ ኣይደለም። ኣይሁዶቹ *የሆሎከስቱን* ፍጅት በታላቅ ሃዘን እንደሚዘክሩት ሁሉ በኦነግ መሪ ድርጅትነት ለመብቱ የሚታገለው የኦሮሞም ህዝብ በወራሪዎች ግፍና ጭካኔ ያለቁ ሚሊዮኖች ዜጎቹን ሊረሳቸው ኣይችልም። እንደማናቸውም የኣለማችን ህዝቦች ሁሉ የኦሮሞም ህዝብ ትላንት ገዢዎች ያቆሰሉትን ኣደገኛ ቁስል መርሳት ከቶ የማይቻለው ነገር ነው።

እንዲህ ማለት ግን ኦሮሞ ለበቀል እየተነሳሳ ነው ማለት ኣይደለም። ኦሮሞ ትላንት ኣይኑን ያጠፋውን ወገን ዛሬ ኣይኑን ኣጥፍቶ ደሙን መበቀል የሚሻ የሃሙራቢ ህግ የሚከተል ህዝብ ኣይደለም። ትላንት እሱን ያቆሰሉት ወንጀለኞች ዛሬ ሙታን ናቸው። የኦሮሞ ህዝብ የመብት ትግል ትላንት ወንጀለኛ የነበሩትን ሙታኖች ቀስቅሶ መዋጋትን ኣላማው ያደረገ ትግል ኣይደለም። ይሁን እንጂ ሙታኖች የሙታንነትን ተፈጥሮኣዊ ህግ ሽረው መንፈሳቸው በልጆቻቸው ኣማካኝነት ዳግም ሲገለጥ መልሱ ዝምታ ሊሆን ኣይችልም። የሙታኖቹ መንፈስ በልጆቻቸው ተመስሎ ብቅ በማለት ተጨማሪ ቁስለት ለማድረስ ጥርሶቹንና ጥፍሮቹን ሲያሾል የኦሮሞ ህዝብ እጁን ኣጣጥፎ ቆሞ ኣይመለከተውም። ይህ ራስን የመከላከል ተፈጥሮኣዊና ኣለም ኣቀፋዊ መብት ኣንዲሁም ህግ ነውና።

ዛሬ "ፍትህ" "ነፃነት" እና "ዴሞክራሲ" በሚሉ ለጆሮ የሚጥሙ ስሞች ራሳቸውን እየጠሩ በተግባር ግን የህዝቦችን የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ መብቶችን ለመደፍጠጥ የሾሚዛቸውን እጅጌ የሰበሰቡ ወገኖች የሙታኑ ልጆች ሆነው በመወለዳቸው ብቻ ወንጀለኞች ኣይደሉም። ወንጀለኛነታቸው ምኑ ላይ እንደሆነ ግልፅ ነው። ወንጀለኛነታቸውን የሚገልፀው የሙታን ኣባቶቻቸውን እኩይ ኣላማና ራእይ ዳግም ኣድሰው ገቢራዊ ለማድረግ ያለሙና ወደጥረቱም የገቡ መሆናቸው ነው። የሙታን ኣባቶቻቸው መናፍስት በነርሱ ስጋ ላይ ነግሰው እያየን ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የሙታኖቹን ወንጀልና በደል በገሃድ ኣውግዘው ተበዳይ ህዝቦችን በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ ፍላጎትና ድፍረት ባልጎደላቸው ነበር። "በርግጥ እኛ "ጀግኖች ኣባቶቻችን" እያልን የምንኮራባቸው ቀደምት ገዢዎች የፈፀሙት ነገር ወንጀል ነበርና ይቅር በሏቸው፣ በትላንት ተፀፅተን በነገ እንካካስ"

እያሉን ኣይደለም ያሉት። እንዲያውም በዚህ ተቃራኒ ሙታን ኣባቶቻችንን ለምን ትቀሰቅሳላችሁ፣ በኣባቶቻችን ደምና ኣጥንት የተገነባችን ሃገር ኣስመልክቶ ለምን ጥያቄ ታቀርባላችሁ፣ የተደራጃችሁለትን ኣላማ ትታችሁ ጭጭ ብላችሁ ለምን የኛን ጎዳና ብቻ ኣትከተሉም በማለት ሙታኖቹን ነፍስ ሊዘሩባቸው ሲሞክሩ ነው የምንታዝባቸው።

እንዲህ ኣይነት ኣሳሳቢ የህሊና ቀውስ ለተጠናወታቸው ወገኖች ኣንድ ግልፅ ነገር እንነግራቸዋለን። ኦነግም ሆነ የኦሮሞ ህዝብ ወይም ሌሎች ማናቸውም የኣለማችን ህዝቦች ስለነገው የሚያስቡት ትላንት ላይ ቆመው መሆኑ ይግባቸው። የታሪክ ኣስፈላጊነቱም ኣንዱ እዚህ ላይ ነው። *"የወጋ ቢረሳ የተወጋ ኣይረሳም'* የሚለው ብሂል የታሪክን ዋጋ ለማስታወስ ጠቃሚ ነው። ትላንት የዛሬ መሰረት ነው። ዛሬም የነገ። ይህ የተፈጥሮ ህግ ነው። ኣንድ ሃይል በድንገት ብድግ ብሎ ሊያፈርሰው የሚችል ህግ ኣይደለም። በርግጥ ስለትላንቱ ዘንግተን ሳይሆን በሆደሰፊነት ይቅር ብለን ኣልፈነው ስለነገው የምናስብበት ሌላ ኣማራጭ ሊኖር ይችላል። ያም ከትላንቱ የወንጀል ጋን እየፈለቀ የሚወጣው ጠንቀኛ ፍሳሽ የነገውን የተስፋ ኣበባ መርዞ ፍሬቢስ ላለማድረጉ ዋስትና ሲገኝ ነው። ያ ዋስትናም የህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተግባራዊነት ነው። ከህዝብ መብቶች በተፃራሪ የተሰለፉ ወገኖች ደግሞ ይህንን መቀበል ይከብዳቸዋል። በህዝቦች በተለይም በብዙሃኑ የኦሮሞ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬና ፍራቻ ስላደረባቸው መብቱ ከቀረበለት ከኢትዮጵያ ተለይቶ የራሱን መንግስት ሊመሰርት ይችላል ብለው በጭፍኑ ይቃወማሉ። ይህንኑን ጥርጣሬ እንደያዙ ደግሞ መለስ ብለው " ለነገሩ ከኦሮሞ ህዝብ መሃል ኦነግን የሚደግፈው ጥቂት ወገን ብቻ ነው" እያሉ ደግሞ ራሳቸውን ለማበረታታት ይጥራሉ። ታዲያ ከኦሮሞ ህዝብ መሃል ኦነግን የሚደግፈው በቁጥር ዝቅተኛ ከሆነ ኦነግ የሚያራምደውን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ተግባራዊነት ለምን ትፈራላችሁ? ድርጅቱን የሚደግፈው ወገን ጥቂት ነው ብላችሁ የለም እንዴ? ተብለው ሲጠየቁ ደግሞ ምላሽ የላቸውም። እንዲያው ግራ ተጋብተው ሌላውንም ግራ ለማጋባት በከንቱ ይደክማሉ።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ትላንት በራሱ ኣላማ ላይ እንደፀና በሆደሰፊነት ኣንዳንድ በኢትዮጵያ ኣንድነት ስም ከሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (AFD)ን በመሰረተበት ወቅት የነበረው የመደማመጥና ይቅር የመባባል ኣዝማሚያ ኣበረታች ነበር። ለኦሮሞና ለሌሎች ህዝቦች ኣንገብጋቢ ጥያቄዎች ትኩረት የሚሰጥ ሁኔታ ነበረ። በመሆኑም ትብብሩ በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ጎራ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ወገኖች ዙሪያ ተቀባይነትን ያገኘና የኣብሮነት ብሩህ ተስፋ የፈነጠቀበት ወቅት እንደነበረ ኣይዘነጋም። ዛሬ በከሰሩ ፖለቲከኞች የተያዘው ሂደት ግን የህዝቦችን የቆየ ቁስል ኣክሞ እንደ ማዳን እንጨት እየሰደደበት ማድማትን መምረጡን ነው የምንታዝበው። የውይይት መድረኩን በማስፋት ፋንታ እጅግ ኣጥብቦት ለኣንድ ወገን ፍላጎቶች ማስተናገጃ ብቻ የሚሆን ቦታ መተውን ነው የምንመለከተው። በዚህ ኣይነቱ ሁኔታ ደግሞ ኣብሮ መሄድና በጋራ መስራት የሚባሉት ነገሮች የማይታሰቡ ናቸው። በዚህ ኣይነቱ የቅልበሳ ጥረት የሚገኝ ውጤትም ቢኖር ኣላስፈላጊ ቀውስና የፖለቲካ ኪሳራ ብቻ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ዋጋ የሚከፍሉት ኣሮጌውን የኣፈና ስርኣት በብልጣብልጥነት ስልት ኣድሰው ለመቀጠል መፍጨርጨርን

**የመረጡ ወገኖች ይሆናሉ። “*ፍትሀ*” “*ነፃነት*” እና “*ዴሞክራሲ*” የሚሉትን ስሞች ለመጠሪያነት በመጠቀም ብቻ ኣፍቃሪ ፍትህ፣ ኣፍቃሪ ነፃነትና ኣፍቃሪ ዴሞክራሲ መባል ኣይቻልም። ስለሆነም በቅድሚያ በስያሜነት ከተመረጡት ሶስቱ ክቡር ቃላት ትርጉም ጋር እርቅ ማውረድ የግድ ይሆናል እንላለን።**

**የኦነግ ኢንፎ ዴስክ**